# ዘመን ወይስ እኛ

ዘመን ቀያየርን አመታት ቆጠርን ፤
በትላንት ማንነት ዛሬም እየኖርን ፤
ጊዜ ተለወጠ ዘመንም ተሻረ ፤
ድንጋያማው ልብም አብሮን ተሻገረ ።
እናም አዲስ አመት ፤
ባልተለወጠ ህይወት ፤
በሙብላት መጠጣት ፤
ደግሞ ተቀበልነው ፤
ለሚቀጥለው አሮጌ ልንለው ፤
እኛ ነን ወይ ዘመን ፤
ማናችን ነው ያረጀን ጊዜ ያለፈብን ።
በወንድሞች መሀል መለያየት በዝቶ ፤
ከፈጣሪ ክብር የራስ ዝና ጎልቶ ፤
በአንድ አምላክ አምልከን ፤
ከአንድ መአድ በልተን ፤
በአንድ አስቀድሰን ፤
ምህላ አድርሰን ፤
እንለያያለን መንታ ልብ አርግዘን ።

ያረጀው ዘመን ነው ፤
ወይስ ልባችን መለወጥ እንቢ ያለው ፤
ፍቅርን እየሰበክን በአደባባይ ቆመን ፤
አንድ መስቀል ስመን ጠበሉን ጠጥተን፤
ከቤት እንደርሳለን ጥላቻን ተሞልተን ።
የሚያስብ ሲጠፋ ለቤተ እግዚአብሔር ፤
በተኩላ ተጠልፎ መንጋው ሲደናበር ፤
መንጋው ሲበታተን እረኛው ተኝቶ ፤
የተጠራበትን ዓላማ ዘንግቶ ፤
ሀብቱን ሲያደላድል ዝና ሲገነባ ፤
መንጋው ቃል ተርቦ ሲጣራ ሲያነባ ፤
የእግዜር ደጅ ተዘግቶ ፤
አለሁ የሚል ጠፍቶ ፤
እንኳን አደረሰህ ዘመን ተለወጠ ዘመኑ አረጀ ፤
እንባባል እኛ በዲያቢሎስ ውግያ መንጋው እየተፈጀ ።

ዮሀንስ ዘርፉ

30/12/2003